የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

(ከመስከረም 28- ጥቅ 5/2017 ዓ.ም)
(October 08- 15/2024)

**1.ኢትዮ ቴሌኮም ለሽያጭ የሚያቀርበውን አሥር በመቶ ድርሻ በቴሌብር ራሱ እንዲያገበያይ ተፈቀደለት**

**ሪፖረተር፡ October 13, 2024**

ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘው ኢትዮ ቴሌኮም ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ለመሸጥ ያቀደውን አሥር በመቶ ድርሻውን፣ የራሱን የቴሌብር መተግበሪያ በመጠቀም ራሱ እንዲያገበያይ ተፈቀደለት።

ከኢትዮ ቴሌኮም ጠቅላላ ሀብት ውስጥ አሥር በመቶ የሚሆነው በአክሲዮን ተከፋፍሎ በሚቀጥለው ሳምንት ከረቡዕ ጥቅምት 6 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ለሽያጭ የሚያቀርብ ሲሆን፣ መንግሥት ቀደም ብሎ በወሰነው መሠረት የኩባንያው አክሲዮኖች ለአገር ውስጥ አክሲዮን ገዥዎች ይሸጣል።

የኢትዮጵያ ሙዓለ ነዋይ ገበያ የኢትዮ ቴሌኮምን አሥር በመቶ ድርሻ በማገበያየት አገልግሎቱን እንደሚጀምር ከዚህ ቀደም ተግልጸ የነበረ ቢሆንም፣ ይህ ዕቅድ ተቀይሮ ኢትዮ ቴሌኮም ራሱ ለሕዝብ የሚያቀርበውን ድርሻ በቴሌብር መተግበሪያው በመጠቀም እንዲያገበያይ እንደተፈቀደለት ለማወቅ ተችሏል።

https://www.ethiopianreporter.com/134279/

**2. የሎጂስቲክስ ዘርፍን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ባለሀብቶች መክፈት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ሥጋት ነው ተባለ**

**ሪፖረትር፡October 13, 2024**

መንግሥት የሎጂስቲክስ ዘርፉን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ባለሀብቶች መክፈቱ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ሥጋት እንደሚፈጥር፣ የኢትዮጵያ የዕቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎች ማኅበር አስታወቀ፡፡

ማኅበሩ ይህንን ያስታወቀው ኢትዮጵያ ከሦስት ዓመታት በኋላ የሚደረገውን ዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ ጉባዔ ለማስተናገድ መመረጧን አስመልክቶ፣ ሐሙስ መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም. ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ ነው፡፡

መንግሥት በሎጂስቲክስ ዘርፉ 49 በመቶ የውጭ ባለሀብቶች እንዲገቡ ሕግ ያወጣ ቢሆንም፣ በቅርቡ ከተደረገው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ወዲህ ግን ዘርፉ ሙሉ ለሙሉ ለውጭ ባለሀብቶች እንዲደሚፈት ማስታወቁ ተገልጿል፡፡

መንግሥት ከአይኤምኤፍ ጋር ባደረገው ስምምነት ዘርፉ እ.ኤ.አ. በ2026 ለውጭ ባለሀብቶች ሙሉ በሙሉ እንደሚፈቅድ ይገልጻል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/134261/

**3. የጤና ተቋማት የመድኃኒት ዱቤ ከባንክ ሒሳብ ተቀናሽ የሚደረግበት አሠራር በአዋጅ ሊፈቀድ ነው**

**ሪፖርተር፡ October 13, 2024**

ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በዱቤ ወስደው ከሦስት ወራት በላይ የሚያቆዩ የጤና ተቋማት፣ ከባንክ ሒሳባቸው ተቀናሽ የሚደረግበት አሠራር በአዋጅ ሊፈቀድ ነው፡፡

ሐሙስ መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም. ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አራተኛ ዓመት የሥራ ዘመን አንደኛ መደበኛ ስብሰባ፣ የመድኃኒት ፈንድና የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ ለማቋቋም በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ለአገልግሎት ከተሰጡ ሥልጣኖች ውስጥ በዱቤ መድኃኒት ወስደው የማይከፍሉ የጤና ተቋማት፣ ከባንክ ሒሳባቸው የመቀነስ ሥልጣን እንዲኖር የሚለው ተካቶበታል፡፡

አገልግሎቱ ከመንግሥት በሙሉም ሆነ በከፊል የሚመደብለት በጀት ስለሌለና ለጤና ተቋማት በዱቤ ለተሰጣቸው መድኃኒት መከፈል ያለበት ክፍያ በወቅቱ መሰብሰብ ካልተቻለ፣ መሠረታዊ መድኃኒቶች ለጤና ተቋማት ባልተቆራረጠ ሁኔታ የማቅረብ ዋና ተልዕኮውን ለመፈጸም እንደሚቸገር ተገልጿል፡፡

የመድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በዘመቻ መልክ ውዝፍ ዕዳ ካለባቸው የጤና ተቋማት መሰብሰብ ያለበትን ሒሳብ ባደረገው ጥረት የተሰበሰበ ሒሳብ መጠኑ ቢቀንስም፣ አሁንም ከ1.2 ቢሊዮን ብር በላይ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ሒሳብ እንዳለው ተገልጿል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/134256/

**5. የቻይናው ኢንዱስትሪ ግሩፕ በገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን መሬት ለማልማት ተስማማ**

**ሪፖርተር፡ October 9, 2024**

የቻይናው ቾንግቺንግ ኩንኋንግ ኢንዱስትሪ ግሩፐ (Chongqing Kunhuang International Industry Group -CKIIG)፣ በስድስት ቢሊዮን ብር (50 ሚሊዮን ዶላር) በገዳ ልዩ የኢኮኖሚ ዞን በንዑስ ተቋራጭነት መሬት ለማልማት ተስማማ፡፡

ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የንዑስ ተቋራጭ አልሚነት ስምምነት የተፈራረመው የቻይና ዓለም አቀፍ ኢንዱስትሪ ግሩፕ፣ በገዳ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ውስጥ ከሚገኘው መሬት 20 ሔክታር የሚሆነውን በማልማት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እንደሚተገብር ታውቋል፡፡

የኢንቨስትመንት ኮሚሽን እንዳስታወቀው ስድስት ቢሊዮን ብር አጠቃላይ ካፒታል ያለው የቻይናው ሲኬአይአይጂ እንዲያለማ የተፈቀደው 20 ሔክታር መሬት፣ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ዩሁንታ ተሰጥቶታል፡፡

thiopianreporter.com/134155/

**6. ኢትዮጵያ የንግድ እና ሰብዓዊ መብት መጠበቅ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን ተፈጻሚነት ለማጠናከር እየሰራች ነው**

**ኢ.ዜ.አ፡ጥቅምት 4/2017**

ኢትዮጵያ የንግድ እና ሰብዓዊ መብት ሚዛንን መጠበቅ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎችን ተፈጻሚነት የሚያጠናክር የድርጊት መርሃ ግብር ወደ ስራ ማስገባቷን አስታወቀች።

በኬንያ ለሶስት ቀናት ሲካሄድ የነበረው ሶስተኛው የአፍሪካ የንግድ እና ሰብዓዊ መብት ፎረም ተጠናቋል።

በፎረሙ ላይ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ43 አፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ 400 የስራ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5292351

**7. የትብብር ማዕቀፍ ሥምምነቱ ወደ ተፈጻሚነት መግባት ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀምን ለማስፈን ያስችላል**

**ኢ.ዜ.አ፡ ጥቅምት 4/2017**

**የናይል ትብብር ማዕቀፍ ሥምምነት ወደ ተፈጻሚነት መግባቱ ፍትሃዊ የውኃ አጠቃቀምን ለማስፈን እንደሚያስችል የውኃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ኃብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) ገለጹ።**

የናይል ወንዝ የትብብር ማዕቀፍ ሥምምነት ከጥቅምት 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ተፈጻሚነት መግባቱን ተከትሎ የውኃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ኃብታሙ ኢተፋ (ዶ/ር) መግለጫ ሰጥተዋል።

በመግለጫቸውም፤ የትብብር ማዕቀፉ ወደ ትግበራ መግባት እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1929 እና በ1959 የተፈረሙትን ኢ-ፍትሃዊ የቅኝ ግዛት ዘመን የውኃ ውሎችን የሚያስቀርና የኢትዮጵያን በውኃ ኃብቷ የመጠቀም መብት የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከ85 በመቶ በላይ ለናይል ወንዝ አስተዋጽዖ ያላት ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች በተፈጥሮ ኃብቷ መጠቀም እንዳትችል ተጽዕኖ ሲደረግባት ቆይቷል ብለዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5291092

**8. የቡናው ዘርፍ ውጤታማ አፈጻጸም – ከልማት እስከ ውጭ ገበያ መላክ**

**ኢ.ፕ.ድ፡ October 9, 2024**

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በሻይ፣ በቡናና ቅመማቅመም ምርቶች ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ ከልማት ጀምሮ እስከ ለውጭ ገበያ /ኤክስፖርት/ ማቅረብና ገበያ ማስፋፋት ድረስ ትርጉም ያለው ሥራ እየሰራ ይገኛል:: በተለይም የእሴት ሰንሰለቱን በመከተል ልማቱ እንዲጨምርና ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ የገበያ መዳረሻዎች እንዲሰፉና የውጭ ምንዛሪ ግኙቱ እንዲያድግ በብዙ እየተጋ ስለመሆኑ እያስመዘገበ ያለው ውጤት ይመስክራል::

ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ከተመረቱ በኋላ ጥራታቸውን ጠብቀው ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ በኩልም በትኩረት ይሰራል:: ለእዚህም የምርት ጥራትን በማስጠበቅና ብክነትን በመከላከል ምርቱ በተሻለ መልኩ ለገበያ እንዲቀርብና የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንዲያስገኝ ይደረጋል:: ከዚህ ጋር በተያያዘ በእሴት ጭመራ ላይም በትጋት በመስራት ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ቡና ምርት ማሳደግና ከቡናው የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማሳደግ ተችሏል:: የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት የአገር ውስጥ ገበያውን ጨምሮ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ምርት በማሳደግ የኢትዮጵያን ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ በማስተዋወቅ ሰፋፊ ሥራዎችን ተሰርተዋል::

https://press.et/?p=138235

**9. የባቡር ትራንስፖርትንና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ለማዘመን ያለመው ሪፎርም**

**ኢ.ፕ. ድ፡ October 12, 2024**

ኢትዮጵያ ወደ ብልፅግና ለመሸጋገር ለምታደርገው ጉዞ የባቡር መሠረተ ልማት ወሳኝ የልማት አንቀሳቃሽ እንደሆነ ታምኖበታል። በመሆኑም ዘርፉን ለማሳደግ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን ላይ ትገኛለች። በሀገር ውስጥ የተጀመሩ የልማት ሥራዎች እንዲሳለጡና ከዓለም ጋር ያላትን የንግድ ትስስር የሚያቀላጥፍና የሚያሳድግ እንደመሆኑም አሁን ያለውን የባቡር መሠረተ ልማት በእጅጉ ለማዘመን ቆርጣ ተነስታለች። ለዚህም እንዲረዳ ስትራቴጂካዊ የሆኑ የአሠራር ሂደቶችን፣ ሕግና መመሪያዎችን በማሻሻል ጭምር እየተንቀሳቀሰች ነው።

በሌላ በኩልም በሀገሪቱ እየተመዘገበ ያለውን ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል የባቡር መሠረተ ልማቱን ከማዘመን ጎን ለጎን የሎጂስቲክ አገልግሎቱንም አቅም በእጅጉ ማጎልበትና አሁን ከሚታይበት የተንዛዛ አሠራር ማላቀቅ ወሳኝ መሆኑም እንዲሁ ታምኖበታል። ለዚህ ደግሞ በተለይም በዘርፉ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ሃገራት ልምድ መውሰድ ተገቢ እንደሆነ እሙን ነው።

https://press.et/?p=138448

## በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

**10. Kurmuk Gold transfers 5.75 million shares to Egyptian company**

**The reporter: October 12, 2024**

Kurmuk Gold has transferred 5.75 million shares to ASCOM Precious Metals Investment Holding BVI, a subsidiary of the Egyptian Asec Company for Mining (ASCOM). A statement released by ASCOM this week confirms the firm has received the shares through its subsidiary. Kurmuk Gold Project is located in the gold-rich Benishangul Gumuz regional state. The shares were transferred to APM through Allied Gold Corp, a Canadian firm behind Kurmuk.

ASCOM, an Egyptian conglomerate affiliated with the government in Cairo, had previously run the Kurmuk project for a decade beginning in 2007 before its license was revoked over security concerns. The license was transferred to Allied Gold Corp in 2017.

https://www.thereporterethiopia.com/42233/

**11. Role of Banks for buttressing economic driv :**

Ethiopian press: October 8, 2024

Financial sectors in Ethiopia have been playing a pivotal role in backing the economic growth and fueling the fight against poverty and underdevelopment. In today's time indeed, the banking sector has become most relevant for everyone as citizens can do their respective transactions from anywhere and at any time through online banking. The Internet has made sending money and transferring funds from one account to another at no cost currently thanks to the proliferation of science and technology.

Taking this fact into account, *The Ethiopian Herald* conducted an exclusive interview with Alemayehu Lemma, an agro-economist graduated from Haramaya University in agro-economics, to receive a professional comment on the role of banks in promoting economic progress.

https://press.et/herald/?p=103562

**12. Engaging of Youth Crucial to Curb Impact of Climate Change on Food Systems, Agroecology: Minister**

**ENA: October 14/2024**

The active engagement of youth is essential in the efforts to curb the severe impacts of climate change on food systems and agroecology in Africa, Ethiopia's Minister of Planning and Development Fitsum Assefa said.

The First Thousand African Youth Summit on Food Systems and Agroecology 2024 is underway in Addis Ababa with the theme "African Youth Showcasing Agroecological Opportunities in Adapting to the Climate Crisis to Address Food System Challenges in Africa."

The First Thousand African Youth Summit on Food Systems and Agroecology 2024 is underway in Addis Ababa with the theme "African Youth Showcasing Agroecological in Opportunities in Adapting to the Climate Crisis to Address Food System Challenges Africa."

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5292273

**13. Economic Development with Human Cost: Balancing Growth and Well-Being**

**Capital: October 14, 2024**

Economic development is often seen as a positive force, driving progress, raising living standards, and fostering innovation. However, while economic growth can bring prosperity, it also has the potential to generate significant human costs, especially when not managed carefully. These costs can take the form of environmental degradation, inequality, social displacement, and the erosion of workers' rights. This article is a humble attempt to explore the often-overlooked human toll that can accompany rapid economic development, providing examples from across the globe and highlighting the need for a more inclusive and sustainable approach.

One of the most visible human costs of economic development is environmental degradation. The pursuit of industrialization, resource extraction, and infrastructure expansion can lead to deforestation, pollution, and the depletion of natural resources. These changes have direct consequences on local communities, particularly those dependent on natural ecosystems for their livelihoods.

https://capitalethiopia.com/2024/10/14

**14. Ethio Telecom to begin selling 10% stake next week**

The reporter: October 12, 2024

Ethiopian carrier Ethio Telecom will kick off its plans to sell a 10 percent stake next week.

The planned sale comes ahead of the company's listing on the country's new stock exchange. Reuters reported this week that the state-owned telco will become the first company to list on Ethiopia's stock market.

From October 16, the public will be able to buy shares on Ethio Telecom's mobile money platform, telebirr.

In an invitation letter sent to the media, Ethio telecom announced the 10 percent stake sales will commence on Wednesday October 16, 2024. The inauguration will be held at Sheraton Addis on the day.

Ethio, which is the incumbent telco in Ethiopia, has long sought private investment.

"This initial public offering will help us to learn and strategize to facilitate the listing of other state-owned enterprises on the Ethiopian Securities Exchange," said Brook Taye, chief executive officer of Ethiopian Investment Holdings.

https://www.thereporterethiopia.com/42216/#google_vignette

**16. Ethiopian Airlines Launches New Route to Port Sudan**

**ENA: October 15/2024**

**Ethiopian Airlines has announced the launch of a new daily flight route to Port Sudan today.**

Ethiopian Airlines Group CEO, Mesfin Tasew said the launch of daily passenger flight to Port Sudan marks the airline's 62nd destination in Africa, underscoring its commitment to expanding its extensive network in Africa.

The new flight will connect the Sudanese people and Port Sudan with Ethiopia and the rest of the world and contribute to the economic development of Port Sudan and promote people to people ties, trade, tourism, and diplomacy, he said.

According to Ethiopian Airlines, the new route will provide seamless travel options for passengers traveling between Ethiopia and Sudan, as well as connecting travelers from across the vast Ethiopian Airlines network to this significant Red Sea port city.

The introduction of this service underscores Ethiopian's dedication to serving the evolving needs of the African market and contributing to the continent's economic development.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5293573